በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር የሕ/ም/ማጠ/ዳ/ 1023/18

ቀን 23/04/2018 ዓ.ም

ለአብክመ ስራና ክህሎት ቢሮ
ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው እንዲሁም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ1 (አንድ) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት የስራና ክህሎት ቢሮ በቁጥር ስ/ለ/ም/ቢ/4/ሚ/85/371 በቀን 30/01/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ "የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አገልግሎት አተገባበር መመሪያ ቁጥር 4/2012 ዓ.ም" ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 መሠረት የተላከለትን መመሪያ ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 24/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲውል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 32...... ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

'ከሰላምታ ጋር'

ሺ.ድጋፍ ኃይሌ
የክልል ዐቃቤ ሕግ


ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትሕ ቢሮ

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ

## የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት አተገባበር መመሪያ



መስከረም 2012 ዓ.ም

ባህር ዳር

## መመሪያ ቁጥር 24/2018

# የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አገልግሎት አተገባበር መመሪያ

አሁን ያለንበት ዘመን አለምአቀፍ የኢኮኖሚ ትስስር የሰፈነበት ሲሆን ኢትዮጵያም የዚሁ ትስስር አካል ናት፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው አለምአቀፍ የገበያ ውድድር ደግሞ ድንበር ዘለል ከመሆኑ የተነሳ በመጪው ጊዜ የገበያው ባለቤት የሚሆኑት በሂደቱ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው አምራቾችና አገልገሎት ሰጪ ተቋማት ናቸው፡፡ ማንኛውም ተቋም ከተወዳዳሪዎቹ ልቆ እንዲገኝ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋነኞቹ በቂ ቴክኒካል ክህሎትና የኢንተርፕሪነርሽፕ ባህሪይ የተላበሰ የሰው ሀይል እንዲሁም ምርጥ ቴክኖሎጂና የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ አሰራር ሲኖር ነው፡፡

ከዚሁ ግንዛቤ በመነሳት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ ተቀርጾ ወደ ስራ ከተገባ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በዚህ ስትራቴጂም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማልማት ከተቀመጡት መንግስታዊ የድጋፍ ማእቀፎች ውስጥ አንዱ ለኢንተርፕራይዞቹ ብቃት ያለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ሲሆን መንግስት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠትና በቀጣይነትም ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲያድጉ በማድረግ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲጠናከርና እንዲስፋፋ የበኩሉን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል፡፡ በዚህም የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው የመሪነቱን ሚና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንደሚወጣ ይጠበቃል፡፡ ይህንን ለማሳካትም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች መካከል አንዱ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ድጋፍ ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ድጋፍ ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ችግር በለየና በፍላጎት ላይ በተመሠረተ የተሟላ መረጃ በማደራጀትና በመስጠት፣ የሥልጠናና ምክር፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ የግብይት፣ የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍ ተግባራትን ባካተተ መልኩ በአራት የድጋፍ ማዕቀፎች ማለትም የካይዘን/የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ/ ድጋፍ፣ የቴክኒካል ክህሎት ድጋፍ፣ የቴክኖሎጂ ድጋፍና የኢንተርፕርነርሽፕ ድጋፍ ላይ መሰረት ተደርጎ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች አማካኝነት

እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን በድጋፉ ጅምር ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም በተግባር አፈፃፀም ሲፈተሽ ሰፊ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን በጥናት ለመለየት ተችሏል፤በመሆኑም ችግሩን በዘላቂነት ለመስፍታትና ውጤታማ ለማድረግ በቀጣይ ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው ድጋፍ አቅም በሚፈጥር፤ በሚያመርቱት ምርትና በሚሰጡት አገልግሎት ምርትና ምርታማነትን በሚያሳድግ፤ በገበያ ውስጥ ብቁና ተወዳዳሪ በመሆን ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥና የኢንዱስትሪው መሰረት እንዲሆኑ ማስቻል ተገቢ በመሆኑ የአመራሩን፤ ባለሙያውን፤ አሰልጣኙንና አንቀሳቃሹን አመለካከትና ክህሎት ከመቸውም ጊዜ በላይ በማሳደግ፤በተዘረጋው አሰራር መሰረት በጥብቅ ዲሲፕሊን በመፈፀምና በማስፈፀም፤ በትኩረት ዘርፎች ላይ በመመርኮዝ ሞዴሎችን በማፍራትና እነሱን ማዕከል አድርጎ ድጋፉን በመስጠት በየደረጃው የሚገኘው አካል በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በተነሳሽነትና በቁርጠኝነት መፈፀም ይገባል። በመሆኑም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራው ተጨባጭ ውጤት በሚያስመዘግብ መልኩ ማከናወን ጊዜ የሚሰጠው ተግባር ባለመሆኑ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በተሻሻለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሰ) ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አገልግሎት አተገባበር መመሪያ ቁጥር 24/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. "ቢሮ" ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኝ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ማለት ነው።

2.2. "የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት" ማለት የኢንተርፕራይዞቹን ችግር የለየና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የተሟላ መረጃ ማደራጀትና የመስጠት፣ ሥልጠናና ምክር፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን በ4ቱ የድጋፍ ማዕቀፎች በመመስረት ለኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የሚሰጥ የተሟላ ድጋፍ ማለት ነው።

2.3. "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ.ህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺ.ህ) ያልበለጠ ካፒታል ያለዉ ኢንተርፕራይዝ ነው።

2.4. "አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ" ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከስድስት እስከ ሰላሳ ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺ.ህ አንድ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺ.ህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺ.ህ አንድ) እስከ 1,500,000 (አንድ ሚልዮን አምስት መቶ ሺ.) ያልበለጠ ካፒታል ያለዉ ኢንተርፕራይዝ ነው።

2.5. "የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና" ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለተሠማሩና ለሚሠማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ባለሙያዎች አንድን ምርት ወይም አገልግሎት በብቃት ለማቅረብ፣ ጥራትና ምርታማነትን በቀጣይነት ለማሻሻል፣ የፈጠራ ሥራዎችን ለማበረታታት አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት በማሳደግ በተሰማሩበት ወይም በሚሰማሩበት መስክ ላይ እሴትን በመጨመር ልማትን ለማፋጠን እንዲያስችል በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች የሚሰጥ ሙያዊ ሥልጠና ነው፣

2.6. "ቴክኖሎጂ" ማለት አንድን ግብዓት በቀላሉ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ቁሳዊ፣ ዕውቀታዊ፣ ሰነዳዊና ድርጊታዊ ክፍሎችን ያካተተ የሥራ ዉጤት ነው።

2.7. "የሙያ ብቃት ምዘና" ማለት አንድ ባለሙያ/አንቀሳቃሽ በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መስፈርት መሰረት የሚጠበቅበትን ብቃት መያዙ የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ በክልል ቢሮ፣ በዞንና ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት፣ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች እና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## 4. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር አገልግሎት ዓላማ

### *4.1. አጠቃላይ ዓላማ*

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስጠት በገበያ ውስጥ በአገልግሎት/ በምርት ጥራት፣ በቴክኖሎጂ፣ በምርታማነት፣ በአሰራርና በዋጋ ተወዳዳሪና ትርፋማ እንዲሆኑ፣ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የላቀ ለውጥ እንዲያመጡ፣ ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩና ገቢያቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው።

### *4.2. ዝርዝር ዓላማዎች*

4.2.1. የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ማስቻል፣

4.2.2. የኢንተርፕራይዞችን የማምረቻ ጊዜ ማሻሻልና ምርታማነታቸውን ማሳደግ፣

4.2.3. የማያቋርጥ የምርትንና አገልግሎት የአመራረት ሂደትን ማሻሻል፣

4.2.4. የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞችን የምርት ወጪን በመቀነስና ጥራትን በመጨመር ትርፋማነታቸውን ማሳደግና የደንበኛን ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ ማርካት፣

4.2.5. ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞችን ክፍተት ከብቃት አሀድ ጋር በማዛመድ ተግባር ላይ እንዲያውሉ በማድረግ የምርታማነታቸውንና የተወዳዳሪነታቸውን አቅም ማሳደግ፣

4.2.6. ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የቴክኖሎጂ መረጣና መቶ ፐርሰንት የቴክኖሎጂ መቅዳት ስራ በመስራት ለጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ማሸጋገር፣

4.2.7. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች የኢንተርፕሪነሪያል አመለካከታቸውን፣ እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን መገንባት፤

4.2.8. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓትን እንዲተገብሩ በማድረግ ትርፋማነታቸውን እንዲጨምሩ ማስቻል፤

4.2.9. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ልማት እውቀትና ክህሎት እንዲያዳብሩ በማገዝ በገበያ ላይ በምርት ጥራት፣ ዋጋና አቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

# 5. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሆዎች፤

1. የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈልፈያና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ፣
2. በገበያ ፍላጎት የሚመራ፣ የተቀናጀና የተዋሃደ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣
3. ግልጽነት፣ተጠያቂነትና ታማኝነት የተላበሰ አገልግሎት መስጠት፣
4. የኢንተርፕራይዞች እድገትና ጥቅም የእኔም ጥቅም ነው ብሎ በማመን መንቀሳቀስ፣
5. ለነባር፤ ሞዴልና በክላስተር ደረጃ ተሰባስበው ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መሰጠት እንዳለበት አምኖ መንቀሳቀስ፣
6. የቴክኖሎጂ አቅምን መገንባት ለኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ መሣሪያ መሆኑን አምኖ መተግበር፣

# 6. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ድጋፍ የማስተግበሪያ ስልቶች፤

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ሲባል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ችግር በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የለየና የተሟላ መረጃ የማደራጀትና የመስጠት፣ ስልጠናና ምክር፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን የሚያካትት ድጋፍ በመሆኑ" የሚከተሉት የማስተላለፊያ ስልቶች ይኖሩታል፤

1. **የካይዘን/የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ/ ድጋፍ፤-** ይህ ድጋፍ የሚሰጠው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብክነትን በማስወገድ፣ወጪን በመቀነስና የስራ ቦታን አመቺ በማድረግ ቀጣይነት ያለው የምርታማነትና የጥራት መሻሻል እንዲያመጡ ለማስቻል ነው።
2. **የቴክኒካል ክህሎት አቅም ግንባታ፤-** ድጋፍም የሚደረገው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች በፍጥነትና በየጊዜው ከሚፈጠሩ የቴክኖሎጂና የገበያ መለዋወጥ ምክንያት የሚያጋጥሟቸውን የቴክኒካል ክህሎት ክፍተቶች ለመሙላት ነው።
3. **የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፤-** ድጋፍ የሚደረገው ለአገራችን ነባራዊ ሁኔታ የሚስማማውንና ተመርጦ መቶ ፐርሰንት የተቀዳውን ቴክኖሎጂ በመውሰድ ውጤታማ የቴክኖሎጂ አብገርዎች እንዲሆኑና በቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ብቁ ተዋናኝ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው።
4. **የኢንተርፕርነርሽፕ አገልግሎት ድጋፍ፤-** የሚሰጠው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የዘመናዊ ንግድ አሰራርን እንዲተገብሩና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቆዩ ለማድረግ ሲሆን በተጨማሪም ዘርፉ በዋነኝነት የስራ እድልን በመፍጠር ኢንተርፕራይዞች ለኢንዱስትሪ ልማት መሰረት መጣል እንዲችሉ ነው።

## ክፍል ሦስት

## 7. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር አደረጃጀት፡-

1. በክልል እና በዞን፤በሜትሮፖሊታንት ከተሞች ደረጃ እንደ ቅደም ተከተላቸው ለዳይሬክተሩ ወይም ለቡድን መሪው ተጠሪ የሆኑ በአምስት ዘርፎች እና የዳታ ቤዝ ባለሙያን በመያዝ የሚደራጅ ይሆናል አደረጃጀቱም ፤-

1.1. የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፤

1.2. የግብርና ዘርፍ (ባለሙያ)፤

1.3. የኮንስትራክሽን አገልግሎትና እደጥበብ ዘርፍ፤

1.4. የቴክኖሎጅ ዘርፍ (ባለሙያ)፤

1.5. የኢንተርፕራይዝ መረጃና ተሞክሮ ቅመራ ዘርፍ፤

1.6. የዳታ ቤዝ ባለሙያ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ/ለቡድን መሪው የሆነ፣

2. ከላይ ከተራ ቁጥር 1.1. እስከ 1.6 በተቀመጠው አደረጃጀት መሰረት የዘርፍ አስተባባሪዎችን እና በየዘርፉ የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በዳይሬክቶሬቱ / በቡድኑ ውስጥ ከሚገኙት ባለሙያዎች በክልል ደረጃ በቢሮ አመራሮችና በዳይሬክተሩ፣ በዞንና ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች ደረጃ በመምሪያ ኃላፊውና በቡድን መሪው የሚመደቡና የሚደራጁ ይሆናል፡፡ የዘርፍ አባላት ብዛት እንደ ሰው ኃይሉ መጠን የሚወሰን ይሆናል፡፡

3. በወረዳ፤በከ/አስተዳደር እና በአንድ ማዕከል ላይ ያለው አደረጃጀት፤ ተግባርና ኃላፊነት በስራ ምዘና እና ደረጃ አወሳሰን ጥናት መሰረት ባለበት የሚቀጥል ይሆናል፤

4. በኮሌጅ ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ቡድን መሪ (ምክትል ዲን) ተጠሪ የሆኑ በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ደረጃ በአራት ዘርፎች እና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ በሁለት ዘርፎች ይደራጃሉ፤-

   4.1. በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ደረጃ በአራት ዘርፍ ማለትም ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፣ ኮንስትራክሽን እና አገልግሎት ዘርፍ፣ ግብርና ዘርፍ እና የቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ በሚል ይደራጃል ፤

   4.2. በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ በሁለት ዘርፍ ማለትም የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ እና የኮንስትራክሽን፤ ግብርና እና አገልግሎት ዘርፍ በሚል ይደራጃል፡፡

   4.3. በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎች ምደባ በተመለከተ ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ትግበራ ተብለው ከተለዩት አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች መካከል ሊያስተባብሩና ዉጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አሰልጣኞችን/ኢንስትራክተሮችን በዘርፍ አስተባባሪዎች ምርጫ፤ ስምሪት አሰጣጥና የጊዜ ቆይታ አወሳሰን አሰራር መሰረት የሚፈፀም ይሆናል ፡፡ይህም ሆኖ ለአስተባባሪነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝ ከሆነ በኮሌጁ ዲኖች የጋራ ውይይት ተደርጎበት በሚደረሰበት የውይይት ድምዳሜ መሰረት ቃለ ጉባዔ ተይዞ በኮሌጁ በኩል እንዲመደብ ይደረጋል፤

5. በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ምክትል ዲኑ ተጠሪ የሆነ አንድ የዳታ ቤዝ ባለሙያ ከአሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች መካከል ተመልምሎ እንዲመደብ ይደረጋል ፡፡ የሚመደበው አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር

በሙያው የተሻለና አቅም ያለው መሆን ይኖርበታል፡ ጥቅማ ጥቅሙን በተመለከተ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር የዘርፍ አስተባባሪዎች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

6. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎች ሊከታተሏቸውና ሊደግፏቸው የሚገባቸውን ዘርፎች በመለየት የመመደብና ስምሪት የመስጠት ተግባር በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ደረጃ ይከናወናል፡፡

7. በፖሊቴክኒክ ኮሌጅና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ የተደራጀው ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎች በሂደት በመዋቅር ጥናት የሚመለስ ሁኖ የደረጃ እድገትና ጥቅማ ጥቅማቸው በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ አስተባባሪዎች ደረጃ መሰረት የሚፈጸም ሆኖ በተጨማሪ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ስራ ስለሚሰሩ የተሰጣቸውን ተግባር ማከናወናቸው በም/ዲኑ አማካኝነት በየወሩ እየተረጋገጠ የተቀመጠውን ወርሃዊ የትራንስፖርት ክፍያ እንዲያገኑ ይደረጋል፡፡

## 8. ተግባርና ኃላፊነት፤

### 8.1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎች

1. የኢንተርፕራይዞችን መረጃ ከአንድ ማዕከል/ጽ/ቤት/መምሪያ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወቅታዊ በማድረግ የማደራጀት፤

2. ለኢንተርፕራይዝ እንቀሳቃሾች በየዘርፉ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አገልግሎት የግንዛቤ መፍጠሪያ ሰነድ የማዘጋጀት፤በየደረጃው እንዲዘጋጅ የማድረግ፤ ግንዛቤ መፍጠርና እንዲፈጠር የማድረግ ፡፡

3. የድጋፍ ፕሮገራሙን መሰረት በማድረግ ድልድል ማካሄድና ፕሮገራሙ ለጽ/ቤት፤አንድ ማዕከል እስከ ኢንተርፕራይዞች ድረስ እንዲደርስ ማድረግ፤

4. የዘርፋቸው እቅድ እንዲዘጋጅ የማድረግ፣ለደጋፊ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች የድጋፍ ስምሪትና ምደባ መስጠት፤ የውጤት ተኮር እቅድ የማውረድ፣ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ ውጤት በመሙላት ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ቡድን መሪው በማቅረብ በቡድኑ የማስገምገምና መጨረሻ በኮሌጁ ሲፀድቅ ለሰው ሀይል የማስገባት፤

5. በወጣው የድጋፍ ፕሮግራም መሰረት ድጋፉ በተቀመጠለት ሰዓትና ቀን እየተሰጠ መሆኑን፣ የሚሰጠው ድጋፍ ሳይንሳዊ አሰራሩን በተከተለ መንገድ መሆኑን፤ ድጋፉ ለዋጭና በዚህ መመሪያ መሰረት እየተፈፀመ መሆኑን በሳምንት ሰስት ጊዜ ከአንድ ማዕከላትና ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጋር በጋራ የክትትልና ድጋፍ ስራ በመስራት የተገኘውን ግኝት በግብረ መልስ ለደጋፊ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች የመስጠትና በግልባጭ፤ ለም/ዲኖች እና ለዲኑ እንዲደርስ የማድረግ፤

6. በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የማስተካከያ ስራ እየተሰራ መሆኑን መከታተልና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ግብረ መልስ የመስጠት፤

7. የኢንዱስትሪ ኤክቴንሽን ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራን ለማስተግበር የተቀመጡ የአሰራር ስልቶች በእያንዳንዱ ድጋፍ ሰጪ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር በተገቢው መንገድ እንዲተገበር የመደገፍና የመከታተል፤

8. ከዘርፉ አንጻር የተዘጋጁ የስልጠና ሰነዶችን ከፍተትን መሰረት ተደርገው መዘጋጀታቸውን መገምገምና የማስተካከያ ስራዎች እንዲሰሩ የማደረግ፤

9. ድጋፍ የሚያገኙት ኢንተርፕራይዞች ከአንድ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር የድጋፍ ቆይታ በኃላ ከየት ወደ የት የእድገት ደረጃ እንደደረሱና ሎሎችንም መረጃዎች ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በመያዝ በቀጣይ ኢንተርፕራይዙን እንዲደግፍ ለተመደበው ድጋፍ ሰጪ አሰልጣኝ/ ኢንስትራክተር በፎርማት ርክክብ የማድረግና የለውጡን ቀጣይነት መከታተል፤

10. የቴክኖሎጅ ኩረጃና ሽግግር ፕሮጀክት ዶክመንት ወደ ትግበራ ከመገባቱ በፊት አስፈላጊነቱና አዋጭነቱ፤ ለኢንተርፕራይዙ ጠቃሚና ተገቢነት ያለው፤ ከጊዜና ከሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች አኳያ የመተግበሪያ አፈፃፀም ዕቅድ የተዘጋጀለት መሆኑ፤ በአጠቃላይ የፕሮጀክት ዶክመንት ይዘትን መሰረት ተድርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ም/ዲኑ፣ የቴክኖሎጅ ባለሙያ/አስተባባሪና የዘርፍ አስተባባሪዎች በጋራ የመገምግምና በመጨረሻም በኮሌጁ ማኔጅመንት አካል በጋራ የማስገምገምና የማስፀደቅ፤ሲፈቀድ ወደ ትግበራ እንዲገባ የማድረግ፤ በትግበራ ወቅት ተገቢውን የክትትልና ድጋፍ ስራ በመስራት ግብረ መልስ መስጠት፤

11. የቴክኖሎጅ ኩረጃውና ሽግግሩ በተፈቀደው ፕሮጀክት መሰረት በተቀመጠለት ጊዜና ሀብት ተግባሩ እየተከናወነ መሆኑን ከዘርፍ አስተባባሪዎችና ም/ዲኑ ጋር በጋራ የመከታተልና ወደ ኢንተርፕራይዞች ተሸጋግሮ ዉጤታማ የማድረግ ስራ መስራት፤

12. በተሰጠ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍና በተሸጋገረው ቴክኖሎጅ የተገኘውን ለውጥ እንዲቀመርና እንዲሰፋ ከወረዳ/ከ/አስተዳደር ጽ/ቤት ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ባለሙያዎች ጋር በጋራ መስራት፤

13. በአጠቃላይ የዘርፍ አስተባባሪዎች በየራሳቸውና በጋራ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የኢንዱስትሪ ኤክቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራው ዉጤታማ መሆኑን መከታተል፤መደገፍ፤ በጋራ መገምገም እና ለውጤታማነት መስራት ፤

14. በም/ዲኑ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡

## 8.2. የዳታ ቤዝ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት፤

1. የኢንዱስትሪ ኤክቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ቡድን ተግባራትን እቅድ የማቀድ፣

2.የኢንተርፕራይዝ መረጃዎችን በትርጓሜና በዘርፍ የማደራጀት፤የማጠናቀርና የመተንተን፤

3. በኢንተርፕራይዝ ደረጃ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ያገኙትን፤ ያላገኙትን፤ መነሻ ፕሮፋይላቸውንና በድጋፍ ሂደት ያመጡትን ለውጥ መረጃ የማደራጀትና የመቀመር፤

4. በየዓመቱ የሚዘጋጁ እሴት ሰንሰለት ትንተናዎች፤የተለዩ ቴክኖሎጅዎች፤ፕሮቶታይፕ የተዘጋጀላቸው፤የተፈተሹ፤ የሰለጠኑ አብዥዎች ፤የተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች፤የተፈራ ሀብት በዓይነትና በመጠን መረጃዎችን የማሰባሰብ፤የማጠናቀር፤ የመተንተን፤ ወደ ዳታ ቤዝ የማስገባትና መረጃ መረብ ላይ የመልቀቅ፣ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፤

5. ለተሸጋገሩ ቴክሎጅዎች ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመነጋገር በጋራ የማስተዋወቅና ገበያ የማፈላለግ፤

6. ሳምንታዊ፤ የ15ቀናት፤ የወር፤ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የማዘጋጀት፤ የማስገምገምና ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ፤በመረጃነት አደራጅቶ በአግባቡ የመያዝ፤

7. ከዘርፍ አስተባባሪዎች ጋር በጋራ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ተግባራትን ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል ፤ በጋራ ይገመግማል ለአጠቃላይ ውጤት በጋራ ይሰራል፤

8. በም/ዲኑ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡

## 9. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አሰጣጥ፤-

9.1. ድጋፍ አሰጣጡ ከተደራሽነት በዘለለ ጥራት ላይ በማተኮር የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥና ዉጤትን በሚያመጣ መልኩ አሰራርና አቅጣጫን በማስቀመጥ መተግበር ተገቢ ይሆናል ። በዚሁ መሰረት በሚከተለው መልኩ የድጋፍ ስርዓት ሆኖ ይተገበራል።

9.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አሰጣጥ በቅድሚያ ለነባር ኢንተርፕራይዞች፤ በክላስተር ማዕከላት ለተሰባሰቡ፤ በትኩረት ዘርፎች (ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ግብርናና አገልግሎት (ካፌና ሬስቶራንት፣ ጋራዥ፣ የሴትና ወንድ ውበት ሳሎን፣ በማንኛውም ጥገና አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ፣ የቱሪስት አገልግሎት፤ግሪነሪና የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገድ) ላይ ሆኖ ሞዴልን በማፍራትና ሞዴልን መሰረት በማድረግ፤ የአንቀሳቃሹን አመለካከት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራትና በመለወጥ ተነሳሽነትና ፍላጎትን የፈጠረና መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል። በክላስተር ማዕከላት የተሰባሰቡ ኢንተርፕራይዞች በማይኖሩበት አካባቢ በተናጠል ውጤትን በሚያመጣ መልኩ ድጋፉ መሰጠት ይኖርበታል።

9.3. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አሰጣጥ ለአንድ ዓመት ከሌሎች ማለትም ከትምህርትና ስልጠና ስራዎች ውጭ ሆኖ በሙያው በተመደበ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ይሰጣል አፈፃፀሙም፤

9.3.1. አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች በተግባራት በጊዜ ገደብ በአንድ አመት ጊዜ ቆይታ (ከሀምሌ 1 እስከ ሰኔ 30) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እና ለትምህርትና ስልጠና በሚል ለሁለት ተከፍሎ በዙር እንዲተገበሩ ይደረጋል፤

9.3.2. በፖሊቴክኒክ ኮሌጅ እና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ በስራ ላይ ካሉት አሰልጣኞች/ ኢንስትራክተሮች ውስጥ በየሙያው ከ30% እስከ 40% የሚሆኑት አሰልጣኞች/

ኢንስትራክተሮች ለ1 (አንድ) ዓመት ጊዜ ቆይታ ከትምህርትና ስልጠና ተግባራት ዉጭ በመሆን በሙሉ ጊዜ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ይሰጣሉ፤ሌሎች ቀሪዎች ደግሞ ለ1(አንድ) ዓመት ጊዜ ቆይታ ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ተግባር ውጭ በመሆን የትምህርትና ስልጠና ተግባራትን በሙሉ ጊዜ ይሰራሉ፤ የአሰልጣኝ/ኢንስትራክተር የስራ ስምሪቱም የደረጃ ዕድገት ለማግኘት ከሚጠበቅባቸው የጊዜ ቆይታ አኳያ ቅደም ተከተላቸውን ታሳቢ በማድረግ እና በሙያው ሊደገፉ የሚችሉ ኢንተርፕይዞችን ብዛት ከግምት ውስጥ በማስገባት በኮሌጁ በኩል እየታየ በየዓመቱ እየተቀያየሩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡

9.3.3. አንድ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር የደረጃ እድገት ለማግኘት የሚጠይቀው የቆይታ ጊዜ ሁለት ዓመት ከሆነ አንድ አመት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት በቀጣይ አንድ ዓመት የትምህርትና ስልጠና ተግባራትን እንዲሰራ ይደረጋል፣ ሶስት አመት የቆይታ ጊዜ የሚጠይቀው ከሆነ አንድ ዓመት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ሁለተኛውን ዓመት የትምህርትና ስልጠና ተግባራትን እንዲሰራ ይደረግና ሶስተኛውን ዓመት በመጀመሪያው አመት ላይ ሲሰራው የነበረውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍን ስራን እንዲሰራ ይደረጋል በተመሳሳይ በመጀመሪያው ዓመት የትምህርትና ስልጠናን ስራ ከሰራ በሁለተኛው ዓመት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በሶስተኛው ዓመት የትምህርትና ስልጠናን ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ውጤቱ የሶስት አመቱ አማካይ ይወሰድና እንዲሞላለት ይደረጋል፡፡ አራት አመት የቆይታ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ በየዓመቱ እየተቀያየረ ሁለት አመት ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ሁለት አመት የትምህርትና ስልጠና ተግባራትን እንዲሰራ በማድረግ ውጤት እንዲሞላ ይደረጋል፡፡

9.4. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት ከተደራሽነትና ከጥራት አኳያ ተጣጥሞ መተግበር ያለበት በመሆኑ በዓመት የኢንተርፕራይዝና የአሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ምደባ ምጥጥን አፈፃፀም ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ይከናወናል፡፡

9.4.1. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ስራ የአሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ምጥጥን በተመለከተ በሙያ የሚገኙ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች ቁጥር እና ከሚደገፉት ኢንተርፕራይዞች ብዛት አኳያ እየታየ ተደራሽነትንና ጥራትን መሰረት በማድረግ ምደባ የሚሰጥ ሆኖ የድጋፍ አገልግሎት ምጥጥኑም 1፤20 አንድ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር በአንድ አመት ሀያ ኢንተርፕራይዞችን ይዞ መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ

በዓመቱ ውስጥ የሚደገፉ ኢንተርፕራይዞች ቁጥርና የድጋፍ ሰጭው አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ብዛት የማይመጣጠም ከሆነ የአሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ስምሪቱ ተጠያቂነትን በተላበሰ፣ብክነትን በማያስከትልና ጥንቃቄ በተሞላበት አግባብ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች እኩል እንዲደርሳቸው በማድረግ 20 ኢንተርፕራይዝ እና ከዚያም በታች እንዲይዙ የሚደረግበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ለድጋፍ አገልግሎት አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች ሲመደቡ በቅድሚያ በዓመቱ የሚደገፉ ኢንተርፕራይዞችን ብዛት ያማከለና ያጣጣመ መሆን ይገባዋል፡፡ ተግባሩም አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ሙሉ የመንግስት የስራ ሰዓትን ተጠቅሞ በአሰራር የተቀመጠውን ሳይንሳዊ የድጋፍ አገልግሎት አተገባበር በመጠቀም ክፍተቶችን የመለየት፣ በክፍተቱ መሰረት ሰነዶችን የማዘጋጀት፣ በተዘጋጀው ሰነድ መሰረት እንቀሳቃሾችን የመደገፍና የማብቃት፣ የድጋፉን ውጤታማነት በተቋማዊና ብሄራዊ የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት የተፈራ ሀብት ለካክ ማንዋል መሰረት የተገኘውን ሀብት የመለካትና በዓመት ውስጥ የተረከባቸውን ኢንተርፕራይዞች ሲረከብ ከነበሩበት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ማሸጋገር ይጠበቃል፤ ሽግግሩም በሰርተፍኬት የተረጋገጠ እንዲሆን ከጽ/ቤቶች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

9.4.2. አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች ሲመደቡ በኮሌጅ ያለውን የስልጠና ዘርፍ፣ አሰልጣኞችን/ኢንስትራክተሮችን እና ኢንተርፕራይዞችን ታሳቢ በማድረግ ከላይ በተራ ቁጥር 9.4.1. በተቀመጠው ምጥጥን መሰረት መተግበር ይኖርበታል፡፡

9.4.3. በኮሌጅ ደረጃ ያሉ ወርክሾፖች፣ቢሮዎች፣ የወርክሾፕ ጥሬ እቃዎች፤ ማሽነሪ፤ የእጅ መሳሪያዎች፣ ግዥዎች፣ የወርክ ሾፕ ሀላፊና አሰልጣኞች /ኢንስትራክተሮች እንዲሁም በኮሌጁ ያሉ ማንኛውም ሀብቶችንና ግብዓቶችን የሚመሩ ባለሙያዎች፤ የዘርፍ አስተባባሪዎች እና ሶስቱም ዲኖች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር እና የትምህርትና ስልጠና ተግባራትን በእኩልነት፤ በፍትሀዊነትና በሀላፊነት ስሜት በማቻቻል እንዲመሩትና በውጤታማነትና በተጠያቂነት እንዲያስተዳድሩት ይደረጋል፡፡

9.4.4. አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት ስምሪት መስጠትና መደገፍ ያለበት በሰለጠነበት ሙያ፤የሙያ ብቃት ምዘና ተመዝኖ በበቃበትና በሚያሰለጥንበት ሙያ ብቻ ይሆናል ፡፡ አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ከሙያው ውጭ

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲሰጥ በዕቅድ አይሰጥም፤ ድጋፍ ላልሰጠ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ውጤት ተኮር አፈፃፀም አይሞላም።

9.4.5. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍና ለቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዉ አፈፃፀም የአሰልጣኞች /ኢንስትራክተሮች በኮሌጅ ደረጃ ስምሪት ሲሰጥ የአሰልጣኙን /ኢንስትራክተሩን ደረጃ ከኢንተርፕራይዙ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ማድረግን ይጠይቃል፣ በዚሁ መሰረት ኢንተርፕራይዞች በትርጉማቸው፤-

9.4.5.1. በትርጓሜ ጥቃቅን ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚሰጠው አሰልጣኝ ደረጃው ሲ የሆነ አሰልጣኝ ይሆናል፤

9.4.5.2. በትርጓሜ አነስተኛ እና ታዳጊ መካከለኛ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚሰጠው ኢንስትራክተር ደረጃው ቢ ወይም ኤ የሆነ ኢንስትራክተር ይሆናል፤

9.4.5.3. በትርጓሜ አነስተኛ እና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ከሌሉ በአሰራራቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ በትርጓሜ ጥቃቅን የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን የቢ ወይም የኤ ደረጃ ኢንስትራክተሮችን በመመደብ እንዲደግፉ ይደረጋል፣

9.4.5.4. የሲ አሰልጣኞች በሌሉበት ኮሌጅ የቢ ወይም የኤ ኢንስትራክተሮች በትርጓሜ ጥቃቅንና አነስተኛ የሚባሉ ኢንተርፕራይዞችን እንዲደግፉ ይደረጋል።

9.4.5.5. ኮሌጁ ድጋፍ በሚሰጥባቸው አካባቢዎች በትርጓሜ አነስተኛ እና ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ኖረው ነገር ግን በኮሌጁ የቢ ወይም የኤ ኢንስትራክተሮች ሳይኖሩ የሲ አሰልጣኞች ብቻ በሚኖሩበት ጊዜ ከሲ አሰልጣኞች መካከል በአቅም የተሻሉትን በመመደብ እንዲደግፉ ይደረጋል፣

9.4.5.6. ከላይ በተራ ቁጥር 9.4.5.5. በተጠቀሰው የምደባ ስምሪት ሥርዓት የሚከናወን ሆኖ የተቀመጠውን አሰራር በውጤታማነት ለመተግበር አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በአሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ወይም በኢንተርፕራይዙ ላይ እንደሚኖረው ክፍተት መጠን ችግሩን ለመፍታት እና ድጋፉን በበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በኮሌጁ በኩል የታመነበት ሆኖ ሲገኝ ዉይይት ተካሂዶበትና ስምምነት ላይ የተደረሰበት ውሳኔ በቃለ ጉባዔ ተመዝግቦ ኮሌጁ እንደ አስፈላጊነቱ የሚሰጠው ተጨማሪ የምደባ ድጋፍ ሊኖር ይችላል።

9.5. የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አሰጣጥ እድገትን መሰረት ያደረገ፤ አዳጊ ብሎም በዘርፉ ሞዴሎችን በመፍጠርና በመጠቀም ላይ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቃል ፡-

9.5.1. ድጋፉ የክህሎት ክፍተትን መሰረት አድርጎ አዳጊ በሆነ መልኩ ክፍተቱ እየተሞላ መቀጠል ይገባል በዚህም መሰረት፤- ከደረጃ አንድ በመነሳት ክፍተቶችን በመሙላት ወደ ደረጃ ሁለት፣ ወደ ደረጃ ሶስት፣ ወደ ደረጃ አራት እና ደረጃ አምስት (ባለባቸው ሙያዎች) መደገፍ፤ ማስመዘን፤ ማብቃትና ከደረጃ ደረጃ በማሸጋገር ማጠናቀቅና በማስመረቅ ከድጋፍ ማዕቀፉ በማውጣት ወደ ቀጣይ የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ በሚቻልበት አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የሙያ ብቃት ምዘናን በተመለከተ በትምህርት ደረጃቸው ከ10ኛ ክፍል በታችና ማንበብና መጻፍ ብቻ የሚችሉ አንቀሳቃሾች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ድጋፉን እስከ ደረጃ አራት በመስጠት ምዘናውን  እስከ ደረጃ ሁለት ድረስ እንዲመዘኑና እንዲበቁ ይደረጋል፡፡

9.5.2. ከካይዘን እና ኢንተርፕርነርሽፕ ድጋፍ አንጻር በትርንሜ ደረጃ ጥቃቅን ጀማሪ ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ አንድ፣ ጥቃቅን ታዳጊ ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ ሁለት፣ ጥቃቅን መብቃት ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ ሶስት፣ አነስተኛ ጀማሪ እና ታዳጊ ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ አራት፣ አነስተኛ መብቃትና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ አምስት በተዘረዘሩት የብቃት አሃዶች በመደገፍ እንዲበቁ ይደረጋል፡፡

9.5.3. ማንኛውም የሲ፣ቢ እና ኤ ደረጃ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ለድጋፍ የተሰጡ ኢንተርፕራይዞችን በደረጃ እድገት ዘመኑ ሁሉንም በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሞዴል የማድረግ፤ ከደረጃ ደረጃ ማሸጋገር ይጠበቅባቸዋል፤ የቢ እና ኤ ደረጃ ኢንስትራክተሮች ለድጋፍ ከተሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ቢያንስ በቁጥር 2 (ሁለት) በደረጃ እድገት ዘመኑ ወደ ታዳጊ መካከለኛ እንዲያሸጋገር በእቅድ ተሰጥቶት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

9.6. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፉ ሞዴልና ክላስተርን መሰረት ባደረገ መንገድ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ይህን ለማድረግ፤-

The ANRS Bureau of Justice

9.6.1. ሞዴል ኢንተርፕራይዙ ውስጥ መሪ አሰልጣኝ ሆኖ ሊሰራ የሚችል አንቀሳቃሽ ማብቃትና በመፍጠር፣

9.6.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፉ በዋናነት ነባር ኢንተርፕራይዞች ላይ በማድረግ የትኩረት ዘርፍ (እድገት ተኮር) የሆኑ ዘርፎችን ቅድሚያ ሰጥቶ በመደገፍ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

9.6.3. ድጋፉን ለኢንተርፕራይዞች ለመስጠት በቅድሚያ ግንዛቤ የመፍጠርና ጠቀሜታውን በማስረዳት ለድጋፍ ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማስቻል መግባባት ላይ በመድረስ ፣በጋራ ዕቅድ መሰረት በውጤታማነት ድጋፉን የመተግበር ፣ ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮዎችን በመቀመር ሌሎች ኢንተርፕራይዞች ሊማሩ የሚገቡትን መለየትና እርስ በርስ በማስተሳሰር ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥና መከታተል ፡፡

9.7. ድጋፉ ሳይንሳዊ አሰራርን በተከተለ መልኩ ከክፍተት ልየታ ጀምሮ የመሙላትና በምዘና የማጠናቀቅ ሂደትን የተከተለ ይሆናል፣ ሙያዊ ክህሎትን በተመለከተ የተደገፉትን አንቀሳቃሾች በተራ ቁጥር 9.5.1. በተመላከተው መሰረት በምዘና ስርዓቱ እንዲያልፉ የማድረግና ከተመዘኑት ውስጥ በየደረጃውም 80 በመቶ የሚሆኑት መብቃት ያለባቸው መሆኑ ታሳቢ ተደርጎ ይሰራል፡፡

9.8. ኮሌጆች ከወረዳ/ከ/አስተዳደር ጽ/ቤቶች ጋር የጋራ ፕሮግራም በመንደፍ በወረዳና ከተማ አስተዳደር ደረጃ በአመት ሁለት ጊዜ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት አርአያ እና ውጤታማ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን በመለየትና የልምድ መለዋወጫ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፣ በዚህም የበላይ አመራሩ እየተገኘ የድጋፍና የክትትል ስራ ይሰራል፡፡

9.9. ካይዘን (ጥራትና ምርታማነት) በተመለከተ በዋናነት ችግሩ ካይዘንን በሙሉ ፓኬጅ አለመተግበርና ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ማድረግ አለመቻል ሲሆን ትግበራውን ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ፦ ካይዘን ራሱን በቻለ ማስተግበሪያ ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር ይገባል፡፡ በዚህም ወሩ በገባ የመጀመሪያው ሳምንት አሰራርና ህግ አድርጎ እንደ ቢሮ፣መምሪያ፣ኮሌጅ፣ ጽ/ቤትና አ/ማዕከል ማወጅና የስራ ቦታ ህጎችን በማውጣት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በትግበራ ማንዋሉ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ካይዘንን ባህል ለማድረግና ለማስቀጠል በዲስፒሊን በመመራት በዋናነት አመራሩ

ከላይ ጀምሮ ትኩረት በመስጠትና በመተግባር እንዲሁም ሁሉንም ሰራተኛ ባሳተፈ መልኩ በዕቅድ እንዲመራ፣እንዲተገበርና ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ባለፈም ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች በአርአያነት መታየት ይገባል፡፡በየወሩ መጨረሻ የካይዘን አስተግባሪ ኮሚቴዉ በቸክ-ሊስት መሰረት የኦዲቲንግ ስራ በመስራት ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

9.10. በኢንተርፕራይዝ ደረጃ የካይዘን ትግበራ አፈፃፀም በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ማዕቀፉ በአሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ እና በኢንተርፕራይዙ ስምምነት በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት በአግባቡ የመተግበርና የማስቀጠል ስራ አጠናክሮ ይሰራል፡፡

9.11. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት በዋናነት የሚሰጠው በኢንተርፕራይዙ የሥራ ቦታ ላይ ከመሆኑ አኳያ ጉልበትን፣ ጊዜንና ገንዘብን የሚጠይቅ በመሆኑና ተግባሩ በተሳካና ዉጤታማ በሚያደርግ መልኩ መከናወን ስለአለበት ለአሰልጣኙ/ ኢንስትራክተሩ የመጓጓዣ አገልግሎት የማቅረብ ወይም ለታክሲ አገልግሎት የሚወጣውን ወጪ መሸፈን ተገቢ በመሆኑ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት በተመደቡበት ጊዜያት ታሳቢ ተደርጎ ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ከኮሌጁ አቅም አኳያ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

9.11.1. ፖሊቴክኒክ ኮሌጆችና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፉ ዉጤታማነት በሚያመች ሁኔታ ለአሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ተሽከርካሪ ወይም ሌሎች አማራጮችን እንዲጠቀሙ በማድረግ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

9.11.2. ከላይ በተራ ቁጥር 9.11.1. የተጠቀሰውን አማራጭ በፖሊቴክኒክ ኮሌጁ ወይም በቴክኒክና ሙያ ኮሌጁ በኩል ማቅረብ የማይቻል ከሆነ አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ለድጋፍ አገልግሎት ስምሪት ተሰጥቶት በሚደግፍበት ጊዜያት (ወራት) ብቻ ተፈፃሚ የሚሆን፤-

9.11.2.1. ከከተሞች ስፋትና ርቀት አኳያ በ10ሩ ነባር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ደረጃ በወር ብር 300 (ሶስት መቶ ብር) የትራንስፖርት ክፍያ ከውስጥ ገቢ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

9.11.2.2. በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እና በአዲስ በተደራጁ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ደረጃ በወር ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) የትራንስፖርት ክፍያ ከውስጥ ገቢ እንዲከፈል ይደረጋል።

9.11.2.3. ክፍያ የሚፈፀመውም አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ በተሰጠው ዕቅድ መሰረት ጊዜውን በአግባቡ ተጠቅሞ ሳይንሳዊ አሰራሩን በመከተል እየደገፈ መሆኑና በዉጤታማነት መንገድ ላይ መሆኑን በሚከታተለው በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ም/ዲኑ ስር በተደራጀው ዘርፍ አስተባባሪ በሚቀርበው አስተያየትና የማረጋገጫ ደብዳቤ መሰረት በም/ዲኑ ፀድቆ በሚመለከተው አካል ክፍያ እንዲፈፀም ይደረጋል።

9.11.3. በቀጣይ የትራንስፖርት ችግሩን ለመቅረፍ ልዩ ልዩ የትራንስፖርት መጓጓገዎችን ማለትም ብስክሌት፣ ባጃጅና ሞተር ሳይክሎች በሂደት እንዲሟሉ በትኩረት ይሰራል።

## 10. ቴክኖሎጅ የመቅዳትና የማሸጋገር ስራዎች፤-

10.1. ቴክኖሎጅ ሲባል፤- ቁስ ብቻ ሳይሆን የአንድ ኢንተርፕራይዝ ችግር የሚፈታና ስራውን ውጤታማ የሚያደርግ እውቀት፣ አሰራርና መሳሪያ ማለት ነዉ። በመሆኑም የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች የኢንተርፕራይዙን ችግር ሊቀርፉና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ከዘርፉ አንጻር ኮድድ የተደረጉ እውቀትና አሰራር ብሎም መስሪያና ማምረቻ መሳሪያ መስራትና ማስተላለፍ እንዳለበት ታሳቢ ተደርጎ የሚፈጸም ይሆናል።

10.2. አራቱ የቴክኖሎጅ ክፍሎች አዋጭነታቸው ተረጋግጦ በራሳቸው ቴክኖሎጅ ሆነው ለኢንተርፕራይዞች ይሸጋገራሉ።

### *10.3. የእሴት ሰንሰለት ትንተና ሰነድ አዘገጃጀትና አፈፃፀም ፤*

10.3.1.በክልል ደረጃ ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከምርምር ተቋማት፤ ከትኩረት መስሪያ ቤቶችና ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች በየዘርፉ በአቅማቸው የተሻሉ አሰልጣኞችን/ኢንስትራክተሮችንና ባለሙያዎችን ወደ ተመረጠ ማዕከል በመሳብ ሞዴል የእሴት ሰንሰለት ጥናት ሰነድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤የተዘጋጀውን እሴት ሰንሰለት ትንተና ሰነድ ወደ ክላስተር መሪ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የማስተላለፍ ስራ ይሰራል፤

10.3.2. የክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ከሚደግፏቸው ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በየዘርፉ በአቅም የተሻሉ አሰልጣኞችን፣ የዩኒቨርስቲ፣የምርምር ተቋማትንና የመሪ መስሪያ ቤት ባለሙያዎችን በማሰባሰብና በመምራት በክላተር ደረጃ ከቀጠናው የልማት ኮሪደር በመነሳትና በክልል ደረጃ የተዘጋጀውን ሞዴል የእሴት ሰንሰለት ጥናት ሰነድ እንደመነሻ በመጠቀም የእሴት ሰንሰለት ትንተና ሰነድ የማዘጋጀትና ቴክኖሎጅዎችን በመለየት በስራቸው ለሚደግፏቸው ኮሌጆች በማውረድ እንዲፈጸም የመደገፍና የመከታተል ስራ ይሰራል፤

10.3.3. የክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ከእሴት ሰንሰለት ትንተና ሰነድ በመነሳት የተለዩና መኮረጅና መሸጋገር ያለባቸውን ቴክኖሎጅዎች ዝርዝር ለቢሮው የማሳወቅ፤ ክልሉ የክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ከተላከለት ዝርዝር በመነሳት ድግግሞሽን በአስቀረ ሁኔታ የክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች የሚኮርጁትንና የሚያሸጋግሩትን ቴክኖሎጅዎች በማሳወቅ እንዲፈፀም ይደረጋል፤

10.3.4. የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የክላስተር መሪ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ከሚያዘጋጁት እሴት ሰንሰለት ትንተና ሰነድ በመነሳት አዋጭ ቴክኖሎጅዎችን እንዲለዩና ከክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ጋር በመናበብ ድግግሞሽን ባስቀረ መልኩ በመኮረጅ እንዲያሸጋግሩ የሚደረግ ይሆናል።

10.3.5. ክልሉና የክላስተር መሪ ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ለሚደግፏቸው ኮሌጆች በየጊዜው በተደራጀና አቅም በሚፈጥር መልኩ የአቅም ግንባታ ፣ተከታታይነት ያለውና የተጠናከረ የድጋፍና ክትትል ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡

10.3.6. የቴክኖሎጅ ሽግግር ስራው የፕሮጀክት ዶክመንት ይዘትን በአሟላ ሁኔታ የራሱ የሆነ የዝግጅትና የትግበራ ጊዜ ተዘጋጅቶለት ማለትም የእሴት ሰንሰለት ጥናት ዝግጅት ፣የቴክሎጅ አዋጭነት መለያና መገምገሚያ፤ የመቅዳት ፣የመፈተሻ፣አብዥ የማሰልጠኛ፣የማሸጋገሪያ እና የሀብት አለካከና የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት የሚካሄድበት ጊዜ በአክሽን ፕላን ተዘጋጅቶ በዘርፍ አስተባባሪዉ ፤ በም/ዲኑ ስር በተደራጀው የቴክኖሎጅ ዘርፍ አስተባባሪ፤ በኮሌጁ በሚገኙ ሌሎች የቴክኖሎጅ ባለሙያዎች እና በማኔጅመንት አካሉ በቃለ ጉባዔ በተደገፈ ተገምግሞና ፀድቆ የሚተገበርና ሂደቱና ውጤቱ እየተገመገመ በዉጤታማነት ይመራል።

10.4. ቴክኖሎጅ ተኮርጆ መሸጋገር ያለበት የኮረጀው አካል አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ በተመረቀበት፣ በተቀጠረበትና በሙያ ብቃት ምዘና ተመዝኖ ብቁ በሆነበት ሙያ ብቻ ይሆናል። ነገር ግን አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ልዩ ክህሎት ኖሮት የፈጠራ ስራ የሚሰራ ከሆነና ከሙያው ውጭ ቴክኖሎጅ ኮርጆ የሚያሸጋግር ከሆነ ቴክኖሎጅው የተሟላ ሰነድ ያለው፣ ፕሮቶታይፕ የተዘጋጀለት፣ የተፈተሸ፣በአእምሮአዊ ንብረት መ/ቤት ቀርቦ እውቅና የተሰጠው፣አብዥ የሰለጠነ እና ተባዝቶ ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የተሸጋገረ መሆን ይኖርበታል። በዚህም ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድ ይኖራል።

10.5. ቴክኖሎጅ ቀድቶ ለማሸጋገር አንዳንድ ቴክኖሎጅዎች በባህሪያቸው የተለያየ የሙያ ዲሲፕሊን የሚጠይቁ በመሆናቸው ቴክኖሎጅን በቡድን ቀድቶ የሚሸጋገርበት ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑና በአፈፃፀሙ አላስፈላጊ የሆኑ ተጠቃሚነቶችንና ክፍተቶችን ለማስወገድ ሲባል በሚከተለው አግባብነት ተፈፃሚ ይሆናል፤-

10.5.1. ከመነሻው የቀረበው የቴክኖሎጅ ፕሮፖዛል ከመኮረጁና ወደ ተግባር ስራ ውስጥ ከመግባቱ በፊት የኢ/ኤ/ቴ/ሽ/ም/ዲኑ፣ የቴክኖሎጅ ዘርፍ አስተባባሪው፤እንዲሁም በም/ዲኑ ስር የተደራጁት ዘርፍ አስተባባሪዎች እና የሚመለከታቸው ሌሎች የቴክኖሎጅ ባለሙያዎች ቴክኖሎጅውን በጋራ ለመኮረጅና ለማሸጋገር የቀረቡ የሙያ ዲሲፕሊኖችን ከአጠቃላይ ቴክኖሎጅዉ ይዘት፣ ከሚኖረው ውስብስብነትና ከሙያ አስተዋጽኦ አንፃር የእያንዳንዱን ዲሲፕሊን ተሳትፎ መካተቱን በቃለ ጉባዔ በማረጋገጥ ለማኔጅመት አካሉ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብና ቴክኖሎጅው በማኔጅመቱ እንዲኮረጅና እንዲሸጋገር በቃለ ጉባዔ በተደገፈ ተገምግሞና ፀድቆ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

10.5.2. አንድ ቴክኖሎጅ ኮርጆ ለማሸጋገር የተለያየ ሙያን የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ እንደ ቴክኖሎጅው ውስብስብነትና ይዘት ብዛታቸው ከ1 እስከ 5 (ከአንድ እስከ አምስት) የሆኑ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች በቡድን ተሳትፈው በተቀመጠው የቴክኖሎጅ ኩረጃና ሽግግር አሰራር መሰረት ተጠብቆ በጋራ አንድ ቴክኖሎጅ የመኮረጅ፣ የማሸጋገር እስከ ሀብት ማፍራት ድረስ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። ይሁን እንጂ ቴክኖሎጅው ተኮርጆ የሚሸጋገረው ከላይ በተራ ቁጥር 10.5.1. በተቀመጠው መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

10.5.3 በቡድን ተቀድቶ በሚሸጋገር ቴክኖሎጅ በተመሳሳይ አንድ ዓይነት ሙያ ከአንድ በላይ አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ተሳታፊ አይሆንም፡፡

10.5.4. የአራቱ ቴክኖሎጅ ክፍሎች በራሳቸው ምንነት፤ አዘገጃጀትና ማሟላት የሚገባቸውንና በቴክኖሎጅ ሽግግር ሂደት የሚፈፀሙ ጉዳዮች በክልል በኩል ሰነዶች ተዘጋጅተው ይወርዳሉ ፤በዚህ አግባብ መሰረት በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ቴክኖሎጅዎች እየተቀዱ አሰራሩን ጠብቀው የቴክኖሎጅ ሽግግር ስርዓቱ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10.5.5. ቴክኖሎጅ ከተቀዳና ለኢንተርፕራይዞች ከተሸጋገረ በኋላ መረጃው ዘላቂ እንዲሆንና በቀጣይም ለመጠቀም ይቻል ዘንድ የቴክኖሎጅ ማቀቢያ ማዕከላት በኮሌጆች ማቋቋም፣ በክልል፤በዞንና በፖሊቴክኒክ ደረጃ የቴክኖሎጅ ዳታ ቤዝ እና ካታሎግ እንዲኖር በማድረግ መረጃው እንዲያዝና ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

10.6. ኢንተርፕራይዞች በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፉ አቀባበል ላይ የሚታየውን የግንዛቤና የአመለካከት ችግርን መፍታት፡-

10.6.1. በተቀናጀ መልኩ ወቅታዊና ለዋጭ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀትና ተጨባጭ ለውጥ ያመጡ ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋት ግንዛቤያቸውንና አመለካከታቸውን መቀየር፤ ማሳደግና ችግር ፈች ድጋፍ ለመስጠት በቅድሚያ አተኩሮ መስራትና እራስን ለዚህ ተልዕኮ ዝግጁና ብቁ ማድረግ፤

10.6.2. ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ውጤታማና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል ከዘርፉ አካያ በሚሰጡ ድጋፎች ላይ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ አገልግሎት የመስጠት ሁኔታን መከተል ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በክልል፤በመምሪያ፤በወረዳ/ከ/አስተዳደር እና በአንድ ማዕከል ደረጃ በማበረታቻነት ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ አገልግሎቶች ማለትም የገበያ ትስስር ድጋፍ ደብዳቤ፣የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ደረጃ ሽግግር፤ የመስሪያና መሸጫ ቦታ ድጋፍ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ድጋፍ፣ ስልጠና የማግኘት (በምስረታ ላይ ከሚገኙት ኢንተርፕራይዞች ውጭ ለሆኑ )፣ ብድር ለማግኘት የሚሰጥ የመልካም ተበዳሪነት ድጋፍ ደብዳቤ ሲሰጥ በቅድሚያ መንግስት በነፃ የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎትን ተቀብለው የተገበሩና በመተግበር ላይ መሆናቸውን

በአንድ ማዕከል በሚገኘው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አመቻች ባለሙያ እና በኮሌጅ ደረጃ ድጋፉ መሰጠቱን በሚከታተለው የዘርፍ አስተባባሪ ጣምራ የማረጋገጫ ደብዳቤ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የሚቀርብ ሆኖ በቀረበው ማረጋገጫ መሰረት በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከሉ በኩል ተረጋግጦና ህጋዊ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህንን ማረጋገጫ የሚሰጡ አካላትም በተጠያቂነት መንፈስ መፈፀም የሚጠበቅባቸው ሲሆን በየደረጃው ያለው የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ መዋቅር ተግባሩ በጥብቅ ዲሲፕሊን እየተፈፀመ መሆኑን የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

10.7. የአሰልጣኙን/ኢንስትራክተሩን፤ አመራሩንና ባለሙያውን አቅም ማሳደግ ፡

10.7.1. በየጊዜው አዳጊ በሆነ መልኩ ለአሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ይገባል፣ ለዚህ አገልግሎትም የሚሆኑ በቀጣይ በተለያዩ ሙያዎች ስፔሻላይዝ የሚያደርጉ የክለስተር መሪ ኮሌጆችን መፍጠርና አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ እየተሳበ ግንዛቤዉ፤ አመለካከቱና ሙያዊ ክህሎቱ በተዘረጉ አሰራሮች ላይ እውቀቱን የሚያሳድግበት ምቹ ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፣ ይህ እስኪሆን ድረስ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር ቅርብ ግንኙነት በመፍጠርና በጋራ በመስራት በአካባቢው በሚገኙ በክላስተር አደረጃጀት በማደራጀት በጋራ እቅድ በመያዝ የአቅም ግንባታውን ስራ ይሰራል፡፡

10.7.2. በየደረጃው የሚገኘውን አመራር የአመራር ስትራቴጅክ አቅሙን ለማሳደግ ስራን በማይጎዳ መልኩ በተከታታይና በፕሮግራም በክረምት ወራት ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

10.7.3. ክህሎቱ፤እውቀቱና አመለካከቱ በአደገ ባለሙያ ተግባራትን በመፈፀም ዉጤታማነትን ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ ከክልል እስከ አንድ ማዕከል የሚገኘውን ፈፃሚ ባለሙያ በየጊዜው ምቹ የአቅም መገንቢያ ስልቶችን እየፈጠሩ አቅሙ የሚያድግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

10.7.4. በቀጣይ ጊዜያት የአሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ቅጥርና ዝውውር በሙያ ዓይነትም ሆነ በመጠን የትምህርት ስልጠናን እና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎትን ያማከለ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

The Amhara ... Bureau of Justice ማርቀቅና ... ዳይሬክቶሬት

## 11. የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### *11.1 የክልል ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ*

1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አስፈፃሚ አካላትን አቅም ማጐልበት፣

2. ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጋር የተገናኙ የወጪ መጋራትንና አሸፋፈንን በተመለከተ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው ክፍልም ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

3. በቴክኖሎጂ አቅርቦት ላይ የሚሰሩ ተቋማት በክልሉ ውስጥ እንዲስፋፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል

4. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎችና የማምረቻ መሣሪያዎች የሚያገኙበትን ሥልት ይቀይሳል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣

5. ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚገኙ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እንዲበረታቱ ያደርጋል፣

6. የቴክኖሎጂ ልማት ስራን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣

7. በክልሉ የሚገኙ የምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ኮሌጆች በምርምር ፕሮግራማቸው ውስጥ የቴክኖሎጂ ልማት ሥራን እንዲያካትቱ ያበረታታል፣

8. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተፈላጊና አዋጭ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች መረጃ፣ዲዛይኖችና ናሙናዎች ያሰባስባል፣ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች አምራቾች እንዲመረቱ ያደርጋል፣

9. የተከረጁና የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች በኤግዚቢሽኖች የሚተዋወቁበት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ሕጋዊ ዕውቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

10. በስሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎች ዲዛይኖችንና ናሙናዎችን እንዲያመርቱ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

11. የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ትምህርታዊ ጉብኝቶችና ሥልጠናዎችን የሚመለከታቸው አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲያገኙ ይከታተላል፣ያመቻቻል፣

12. በክልል ለሚሰራው የሰው ኃይል ልማት፣ቴክኖሎጂ አቅርቦትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አስፈላጊውን ማንዋል ዝግጅት ፤በጀትና የሰው ኃይል እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

13. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ቴክኖሎጅ ሽግግር አደረጃጀትን ያደራጃል ባለሙያዎች ያስመድባል፣

14. የቴክኖሎጂ ልማት ስራን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣

15. ለቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች የክህሎት ክፍተታቸውን በማጥናት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከፌደራል ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኤጀንሲና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለኢንስትራክተሮችና ባለሙያዎች በቴክኖሎጅ መቅዳትና ማሸጋገር ሥልጠና መስጠት፤

16. በሥሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንተርፕርነርሽፕ አቅም፤ ካይዘን አቅም፤ የቴክኖሎጅ አቅምና የቴክኒካል ክህሎት አቅም ስልጠና ብቃታቸው በተረጋገጠ አሰልጣኞች እንዲሰጥ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

17. ስለ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዎች አተገባበር ስኬቶች ለኮሌጆች፣ ለዞን እና ከተማ አስተዳደር መምሪያዎች የሱፐርቪዥን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፡፡

### *11.2. የዞን /ከ/አስተዳደር ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት መምሪያ*

1. ስለ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አስፈጻሚ አካላትና ሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጥና ሰፊ የማስተዋወቅና የሕዝብ ግንኙነት ስራ መስራት፣

2. በዘርፉ የተሠማሩ ባለሙያዎችን አቅም ማጐልበትና በዞኑ ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ተቀናጅተው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

3. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ማጠናቀር፣ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት ማስተላለፍ፣

4. በሥሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንተርፕርነርሽፕ አቅም፤ካይዘን አቅም፤የቴክኖሎጅ አቅም እና የቴክኒካል ክህሎት አቅም ስልጠና ብቃታቸው በተረጋገጠ አሰልጣኞች እንዲሰጥ ያስተባብራል፣ይመራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

5. ስለ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዎች አተገባበር ስኬቶች ለፖቴክኒክ ኮሌጆች፣ ቴክኒክ ኮሌጆች፣ ለወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤቶች የሱፐርቪዥን ድጋፍ ፤ ክትትል ማድረግና ግብረ መልስ የመስጠት ፡፡

6. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ተግባሩ በዞኑ ውስጥ ያመጣውን ዉጤትና ፋይዳ በዳሰሳ ጥናት የመለየትና ላጋጠሙ ችግሮች የመፍትሄ ሰሃቦችን በማስቀመጥ የመተግባር፤

## *11.3. የከተሞችና ወረዳዎች ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት*

1. ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ተቀናጅተው ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ የምክርና የግንዛቤ ፈጠራ አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የኢንተርፕራይዞችና አንቀሳቃሾችን መረጃ ማሰባሰብ፣ ማጣራት፤ ማጠናቀርና ለሚመለከታቸው ማስተላለፍ፣ በየጊዜው መከለስ፣ እንዲሁም ግንዛቤ መፍጠር፤

2. ከቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጋር በመቀናጀት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆን መከታተልና መደገፍ ፤የሚገፉትን ኢንተርፕራይዞች

በትንሚና በዘርፍ በመለየትና የተሟላ ሰነድ በማዘጋጀት ዝርዝራቸውን ለኮሌጅ ያስተላልፋል፤ መደገፋቸውን ይከታተላል፤ለውጤታማነት በጋራ ይሰራል፤

3. ሪፖርቶችንና መረጃዎችን ማጠናቀርና ለበላይ አካላት ማስተላለፍ፣

4. በሥራው የተሻለ ብቃት ያላቸውንና ውጤት ያስመዘገቡ ሠራተኞችን ማበረታታት፡ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ በመቀመርና በዓመት ሁለት ጊዜ ፕሮግራም በማዘጋጀት የተሞክሮ ልውውጥና ማስፋት ስራ ይሰራል፤

5. ስለ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና ቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዎች አተገባበር ስኬቶች ድጋፍ ለሚያደርጉት ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጆች፤ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፤ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሙያዎች የሱፐርቪዥን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፤ግብረ መልስ የመስጠት፡፡

6. በወረዳ/ከ/አስተዳደር የሚገኙ የሚመለከታቸውን የካቢኒ አመራሮችንና የኮሌጅ ቦርድ አማራሮች የኢንዱ/ኤክስቴንሽን ድጋፍ ወጥና ተከታታይነት ያለው መርሐ ግብር በማዘጋጀት ክትትል ድጋፍና ግምገማ በማድረግ የማስተካካያ እርምጃም እንዲወስዱ ያስተባብራል፤

## *11.4. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ*

1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለምን፤እንዴት፣ የትና በማን እንደሚሰጥ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት፣

2. የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን በመስፈርቱ መሰረት መመልመል፣

3. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በተሟላ ደረጃ ያደራጃል፣ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡ የኢንተርፕራይዞችንና አንቀሳቃሾችን መረጃ ማሰባሰብ፣ ማጣራት ማጠናቀርና ለሚመለከታቸው ማስተላለፍ፣ በየጊዜው መከለስ፣ እንዲሁም ግንዛቤ መፍጠር ፤

4. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ችግሮች በየጊዜው መረጃዎችን በማሰባሰብ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ የሚፈቱትን ለቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ያስተላልፋል፣

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትሕ ቢሮ
The ANRS Bureau of Justice
የህግ ምርምር ማርቀቅና ማጠናቀር ዳይሬክቶሬት

5. በየወቅቱ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሚሰጡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ሪፖርት ይቀበላል።

6. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤ ያመቻቻል፤ ድጋፉ በተቀመጠለት ፕሮግራም መሰረት መሰጠቱን ይከታተላል፤ ከተጠቃሚዎች ግብረ መልስ ያሰባስባል ለወረዳው፣ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፤

## *11.5. የፖሊ ቴክኒክ / ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ*

1. ለኢንተርፕራይዞች የተሟላና ለውጤታማነት የሚያበቃ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር (በኢንተርፕርነርሽፕ፤ በካይዘን፤ በቴክኖሎጅና በቴክኒካል ክህሎት) የድጋፍ ስልቶች መሰረት ሳይንሳዊ ሂደቱን ተከትሎ የተሟላ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፤ ቴክኒካል ክህሎት ድጋፉ በምዘና እንዲቋጭ ያደርጋል፤

2. አዋጭ ቴክኖሎጂዎች በመተንተን፤ በመምረጥ፣ ዲዛይንና ናሙና በማዘጋጀትና ፈትሾ በማረጋገጥ ለአብኝዎች ስልጠና በመስጠት እንዲሸጋገርና ሀብት እንዲያፈሩ ያደርጋል፣

3. ለሰው ሃይል ልማት፣ለቴክኖሎጂ አቅርቦትና ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በስልጠና ማንዋል መሰረት ስልጠና ይሰጣል ፤አቅም ይገነባል፤

4. ሞዴሎችን በማፍራት፤ቅድሚያ በትኩረት መስክ ለተሰማሩና በክላስተር ደረጃ ለሚገኙ ነባር ኢንተርፕራይዞች ላይ ትኩረት አድርጎ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፣

5. የመሳሪያ ኪራይ አገልግሎት መስጠትና የመለዋወጫ ዕቃዎችን በመኮረጅ በአካባቢያቸው ለሚገኙ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተመጣጣኝ ዋጋ በሽያጭ ያቀርባል ፤

6. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትና ቴክኖሎጅ ሽግግር አሰልጣኞችን/ ኢንስትራክተሮችን፤ ባለሙያዎች ያስመድባል፣

7. በሊዝ ፋይናንስ ማሽነሪ ለወሰዱ ኢንተርፕራይዞች የጥገና አገልግሎት የሚሰጥበትን መንገድ ያመቻቻል፤የጥገና አገልግሎት ይሰጣል፤

8. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ችግሮችና ክፍተቶች በተመለከተ ዝርዝር ጥናት ያደርጋል፣

9. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ስለ ቴክኖሎጂና ማምረቻ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ አያያዝና ጥገና ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

10. መረጃዎችንና ሪፖርቶችን ማጠናቀርና ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፣

### *11.6. በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከተጠቃሚዎች የሚጠበቁ ኃላፊነቶች*

1. በሙሉ ፍላጎት ብቻ ተመስርቶ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን፣

2. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ አካልም ሆነ ለሌላ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው አካል ትክክለኛ መረጃ መስጠት፣

3. ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪው አካል ጋር በተዘጋጀው የድርጊት መርሀ-ግብር እና የአገልግሎት የውል ስምምነት መሠረት የድርሻውን መወጣት፣

4. ህጋዊ ባልሆነ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለመሳተፍ፣

6. ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጠው አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ጋር በድጋፍ አገልግሎት ውል ከተቀመጠው ውጪ ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት ያለመፍጠር፣

7. ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጠው አሰልጣኝ/ኢንስትራክተር ጋር የገባውን ቀጠሮ የማክበር ችግር ካጋጠመውም አስቀድሞ የማሳወቅ::

## 12. የክትትል ድጋፍ ስርዓት

1. በኮሌጅ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጅ ሽግግር አፈፃፀም በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ቡድን ደረጃ በየሳምንቱ፤ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ አስተባባሪዎች በዘርፋቸው ካለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎችና ድጋፉን የሚሰጡ አሰልጣኞች/ኢንስትራክተሮች ጋር በድጋፍ አሰጣጡና ውጤታማነት ላይ በየ15ቀናት የጋራ ክትትል፤ ድጋፍና ግምገማ በማድረግ ይመራል፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ
The ANRS Bureau of Justice
የህግ ምርምር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት

2. በኮሌጅ ማኔጅመንት ደረጃ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጅ ሽግግር ድጋፍ አሰጣጥና አፈፃፀም ላይ በየ15 ቀናት እየተገመገመ፤ በዉጤታማነት እየተለካና እየተመራ ለወረዳዉ/ለከ/አስተዳደሩ ጽ/ቤት በጽሁፍ ሪፖርት ይደረጋል፤

3. ወረዳዉ/ከ/አስተዳደሩ ከኮሌጅ በተላከለት ሪፖርት፤ በራሱ የመስክ ክትትልና ድጋፍ መነሻነት ከኮሌጅ ጋር በየ15 ቀናት በጋራ ይገመገማል፤ በጋራ የተገመገመና ተናባቢ የሆነ ሪፖርት በየ15 ቀናት ለዞን መምሪያ፤ የዞን/ከ/አስተዳደር መምሪያ በየወሩ የተገመገመ የጽሁፍ ሪፖርት ለክልል ያደርጋል፤ ሁሉም በተዋረድ ለሚደግፈዉና ለሚከታተለው አካል ወርሀዊ ግብረ መልስ ይሰጣል።

4. በአንድ ማዕከል ደረጃ ከኮሌጅ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪዎች ጋር የጋራ ፕሮግራም በማዘጋጀት በሳምንት ሶስት ቀን፤ በኮሌጅ እና በወረዳ/ከ/አስተዳደር ደረጃ በተናጠል ወይም በጋራ በሚዘጋጅ ፕሮግራም በየ15 ቀናት፤ በዞን እና በክልል ደረጃ በየወሩ በፕሮግራም በታገዘ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ስራ ይሰራል፤ግብረ መልስ ይሰጣል፤

5. ክልል፤ ዞንና ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች በጋራ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጅ ሽግግር ውጤታማነት ላይ ያተኮረ በዓመት አንድ ጊዜ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ቀርቦ ውይይት ይደረጋል፤

4. በአስተዳደር እርከን ተዋረድ የመስክ ድጋፍና ክትትል ስራን አጠናክሮ በማስቀጠል ተጨባጭ ዉጤታማነትን ማረጋገጥ ይገባል።

5. አመራሩ፤ባለሙያውና አሰልጣኙ/ኢንስትራክተሩ ለተግባሩ ውጤታማነት በቁርጠኝነትና በጥብቅ ዲሲፕሊን በመምራትና በመተግባር ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ ይገባል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው /መ/ቤት /ድርጅት ይህን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ ከቢሮውና ከተዋረድ አካላቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

14.ስለተጠያቂነት

ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ከዚህ መመሪያና ከአሰራር ውጭ የሚፈፅም አካል አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

15.የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎችና የተለመዱ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

16. መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

17. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 01 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ያሽምበል ከበደ አስረስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ

ባህር ዳር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍትሕ ቢሮ The ANRS Bureau of Justice የህግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠናቀቅ ዳይሬክቶሬት